መመሪያ ቁጥር 05/2015

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ እና ወደ ክላስተር ማዕከላት ለሚገቡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ ወይም መሬት መጠን ለመወሰን እና ለመስጠት ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ

በክልላችን ሥራ ፈላጊ ወጣቶች በሥራና ስልጠና ቢሮ ተደራጅተው የተለያዩ ድጋፎችን በማግኘት የተሻለ ሀብት ሲያፈሩና የሥራ ዕድል ሲፈጥሩ ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ እና በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም ድጋፍና ክትትል ደግሞ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ እንዲሁም ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪ በመሸጋገር የአገሪቱን እና የክልሉን ኢኮኖሚ ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ እንዲችሉ ማድረግ በማስፈለጉ፤

ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከ2007 ዓመተ ምህረት በፊት እንደ የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ከ500 ካ.ሜ ጀምሮ የመስሪያ ቦታ በምደባ ይሰጥ ስለነበር እና የቦታ አሰጣጡ የኢንዱስትሪዎችን የማምረት አቅምና የፕላንትና ማሽን ላይ አውት መሠረት ያላደረገ በመሆኑ ለአንዳንዶች የቦታ ጥበትን ሲያስከትል ለአንዳንዶች ደግሞ የቦታ ብክነትን የፈጠረ በመሆኑ፤

መንግሥት ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንደማንኛውም ባለሀብት ፕሮጀክት ቀርፀው መወዳደር ይችላሉ የሚል አቅጣጫ አስቀምጦ ሲሰራ የቆዩ ቢሆንም ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩት ከከፍተኛ ኢንዱስትሪዎች ጋር መወዳደር ባለመቻላቸው መወዳደር የሚችሉበትን ሁኔታ ማስቀመጥ በማስፈለጉ፤

ቀደም ሲል ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ የተሸጋገሩ እና ወደ ክላስተር ማዕከላት መግባት የሚችሉ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በመመሪያ ቁጥር 01/2013 ብቻ ሲታይ የቆየ ቢሆንም ከመመሪያው ስፋትና ከያዘው መስፈርት አንጻር ሲታይ አብሮ የማይሄድ ስለሆነ፤

ቀደም ሲል በቢሮው የተዘጋጀው መመሪያ ቁጥር 02/2013 በትግበራ ወቅት በተነሱት ጥያቄዎች መሰረት መብራራት፣ መካተትና መሻሻል ያለባቸው አንቀጾች በመኖራቸውና ከወቅቱ ነባራዊ ሁኔታ ጋር እንዲሄድ ማድረግ ተገቢ በመሆኑ፤

አዲሱ የአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ለቢሮው ከሰጠው ተግባርና ኃላፊነት አንጻር የተገናዘበና ለኢንቨስትመንት ፍሰቱ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር በማስፈለጉ፤

በዘርፉ የተሰማሩ አነስተኛና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ሀብት እንዳያፈሩና ለውጥ እንዳያመጡ እንቅፋት የሆነባቸውን የመስሪያ ቦታ ችግር መፍታት ተገቢ በመሆኑ፤ በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት የተሻሻለው የአስፈፃሚ አካላትን እንደገና ማቋቋሚያና ስልጣንና ተግባራትን ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 280/2014 አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀጽ 1(ሰ) ለኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በተሰጠው ሥልጣን መሰረት ይህን መመሪያ አሻሽሎ አውጥቷል፡፡

ክፍል አንድ
ጠቅላላ

1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ “ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ እና ወደ ክላስተር ማዕከላት ለሚገቡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በያዙት የሥራ ዘርፍ የመስሪያ ቦታ ወይም መሬት ለመወሰንና ለመስጠት ተሻሽሎ የወጣ መመሪያ ቁጥር 05/2015” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

2. ትርጓሜ

የቃሉ አግባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ፡-

1) “**አዋጅ**” ማለት በፌደራሉ መንግሥት የወጣው የኢንቨስትመንት አዋጅ ቁጥር 1180/2012 ነው፤
2) “**ቢሮ**” ማለት የአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮና በስሩ የተደራጁ መዋቅሮቹንም ይጨምራል፤
3) “**ኮርፖሬሽን**” ማለት የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ኢንዱስትሪ ፖርኮች ልማት ኮርፖሬሽንና በስሩ የተደራጁ መዋቅሮቹንም ይጨምራል፤
4) “**የኢንዱስትሪ ክላስተር ማዕከላት**” ማለት ከሁለገብ ኢንዱስትሪና ከተቀናጀ ኢንዱስትሪ ፓርክ ጋር ትስስር ሊፈጥር የሚችል የኢንዱስትሪ ዕድገትን የሚያፋጥኑ እንደ መንገድ፣ ውኃ፣ ቴሌ፣ የኤሌክትሪክ ኃይል፣ የአንድ ማዕከል አገልግሎት እና የመሳሰሉት አስፈላጊ የመሰረተ-ልማት አውታሮች ተሟልተውለት ጥሬ እቃዎችን ተቀብሎ በከፊል ያለቀለት ምርት ሊያምርቱ የሚችሉ አነስተኛና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎችን ለማልማት የሚቋቋምና ወሰን ያለው ቦታ ሁኖ ከዚህ በፊት ለአነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታተብሎ የተገነቡ ህንጻዎችና ሸዶችን ይጨምራል፤
5) “**ሁለገብ ኢንዱስትሪ ፖርኮች**” ማለት ከተቀናጀ የኢንዱስትሪ ፖርክ ውጭ ያለ ሆኖ ሁሉም አይነት ኢንዱስትሪዎች የሚቋቋሙበት፣ በየዘርፎቻቸው የሚደራጁበትና አስፈላጊ መሰረተ ልማት የተሟላለት የኢንዱስትሪ ክላስተር ወይም የኢንዱስትሪ ዞንን እና የኢንዱስትሪ ሸዶችን የያዘ ፖርክ ነው፤
6) “**ሸድ**” ማለት ወደፊት እንደ ሁኔታው ግንባታውን በባለቤትነት በሚያካሂደው ድርጅት ወይም በቢሮው በሚገለጽ ዝርዝር ዲዛይን ወይም አሰራር መሰረት የአምራች ሃይሉን፣ የማምረቻ ማሽኖችን፣ ሌሎች ቁሳቁሶችን ወዘተ በማቀናጀት የኢንዱስትሪ ምርት

ለማምረት፣ ለመሸጫና ምርት ማሳያ የሚውልና ለዚሁ ዓላማ እንዲያመች ሆኖ ለኪራይ ዓላማ የተገነባ ወይም የሚገነባ ህንፃ ነው፤

7) **“ያለቀለት የኢንዱስትሪ ምርት”** ማለት ማሽንን ወይም መሳሪያን ተጠቅሞ ጥሬ ዕቃን ወይም በከፊል የተቀነባበረ የኢንዱስትሪ ውጤትን በማቀነባበር የመጠን፣ የቅርፅ ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግና በማሻሻል ለውጭ ወይም ለሀገር ውስጥ ገበያ የሚቀርብ ምርት ነው፤

8) **“በከፊል ያለቀለት ምርት”** ማለት ማሽንን ወይም መሳሪያን ተጠቅሞ ጥሬ ዕቃን በመጠቀም የመጠን፣ የቅርፅ ወይም የይዘት ለውጥ በማድረግና በማሻሻል ለሌሎች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚያገለግል ምርት ነው፤

9) **“አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪ”** ማለት የኢንዱስትሪዉን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ11 እስከ 50 ሰዎችን በቋሚነት የሚያሰማራና የጠቅላላ ሃብት መጠኑ ከብር ከ600,001 ብር እስከ 10,000,000 ብር (ከስድስት መቶ ሽህ አንድ ብር እስከ አስር ሚሊዮን ብር) የሆነ ኢንዱስትሪ ነዉ፤

10) **“መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪ”** ማለት የኢንዱስትሪዉን ባለቤት፣የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ ከ51 እስከ 100 ሰዎችን በቋሚነት የሚያሰራና የጠቅላላ ሃብት መጠኑ ከብር ከ10,000,001 ብር እስከ 90,000,000 ብር (ከአስር ሚሊዮን አንድ ብር እስከ 90 ሚሊዮን ብር) የሆነ አምራች ኢንዱስትሪ ነዉ፤

11) **“ከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪ”** ማለት የኢንዱስትሪዉን ባለቤት፣ የቤተሰቡን አባላትና ተቀጣሪ ሰራተኞችን ጨምሮ 100 ሰዎችን በቋሚነት በላይ የሚያሰራና የጠቅላላ ሃብት መጠኑ ከብር ከ90,000,000 ብር (ዘጠና ሚሊዮን ብር) በላይ የሆነ አምራች ኢንዱስትሪ ነዉ፤

12). **“የኢንዱስትሪ ደረጃ ሽግግር”** ማለት አንድ ኢንዱስትሪ ባለበት ደረጃ የሚሰጠውን ድጋፍ ተጠቅሞ በካፒታልና በሰው ኃይል መጠን ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ፣ ከመካከለኛ ወደ ከፍተኛ መሸጋገር ሲችል ነው፤

13) **“የውጭ ምርት”** ማለት በአገር ውስጥ ኢንዱስትሪዎች ተመርቶ ለውጪ ገበያ የሚቀርብ ሸቀጥ ወይም ምርት ነው፤

14) **“ማሽን ለይ አውት”** ማለት ለምርት ማምረቻ የሚስፈልጉ ማሽኖች የሚያርፉበት፣ ለዕለታዊ ፍጆታ የሚሆኑ ጥሬ ዕቃዎች የሚቀመጡበትና ለሰራተኛው እንቅስቃሴ የሚያስፈልግ የቦታ/መሬት መጠን በካሬ ሜትር ስፋት ነው፤

15)“**ፕላንት ለይ አውት**” ማለት በአንድ ፋብሪካ ውስጥ ያሉትን የማምረቻ ክፍሎች፣ የማምረቻ ማሽኖች፣ ቁሳቁሶችን፣ አገልግሎት የሚሰጡ ክፍሎችን ማለትም የጥሬ ዕቃ ማስቀመጫ፣ የምርት ማስቀመጫ፣ የጥገና ክፍል፣ መጫኛና ማውረጃ ቦታን፣ የአስተዳድር ቢሮ፣ የስልጠና ክፍል፣ የአትክልት ቦታን፣ ለሰራተኛ አስፈላጊ የሆኑ ክፈሎችን ማለትም ሽንት ቤት፣ የማረፊያ ክፍል፣ የህክምና ክፍል፣ ሎከር፣ የመዝናኛ ክፍል የጥበቃ ክፍል፣ የመኪና ማቆሚያ የመሳሰሉትን በስርዓት በማደራጀት ለእያንዳንዱ ክፍልና ማሽነሪ የሚያስፈልገውን የቦታ ስፋት በማስላት ፋብሪካው በምርት ጥራትም ሆነ ብዛት ወጤታማ እንድሆን የሚያስችል የቦታ አደረጃጀት ነው፤

16)“**አምራች ኢንዱስትሪ**” ማለት ማንኛውም የንግድ ተግባር ሆኖ በሞተር ሀይል የሚንቀሳቀስ ወይም ለማምረት የሚያገለግሉ ግባአቶች፣ ማሽን፣ ቴክኖሎጂ እና የሰው ኃይል በመጠቀም ምርት የማምረት እና አገልግሎት መስጠትን ይጨምራል፤

17)“**ቋሚ የሥራ ዕድል**” ማለት በማናቸውም ኢንዱስትሪ ውስጥ ሥራ ላይ የተሰማራ የቤተሰብ አባላትን ጨምሮ ከአንድ ዓመትና በላይ ላላነሰ ጊዜ የሙሉ ጊዜ ተቀጣሪ በመሆን በፔይሮል የደምወዝ ክፍያ በማግኘት የሥራ ዕድል የተፈጠረላቸው ነው፤

18)“**ገምጋሚ ኮሚቴ**” ማለት በቢሮ እና በስሩ በተደራጁ መዋቅሮች ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ እና ወደ ክላስተር ማዕከላት ለመግባት ጥያቄ ለሚያቀርቡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ ወይም መሬት እንዲሰጣቸው ያቀረቡትን ጥያቄ መነሻ በማድረግ የመስሪያ ቦታ ወይም መሬት መጠን ገምግሞ የውሳኔ ሀሳብ ለማቅረብ የተቋቋመ ኮሚቴ ነው፤

19)“**ባንክ ትራንዛክሽን**” ማለት በፋይናንስ ተቋም ውስጥ በተወሰነ ጊዜ የሚታየውን የገንዘብ ገቢና ወጭ በማስላት የባለሀብቱን አቅም ለማወቅና ጤናማ የሆነ የገንዘብ እንቅስቃሴ መኖሩን ለማረጋገጥ የሚጠቅም ሰነድ ነው፤

20) “**ባለሀብት**” ማለት ኢትዮጵያ ውስጥ ካፒታል ሥራ ላይ ያዋለ የአገር ውስጥ ወይም የውጭ ባለሀብት ነው፤

21) “**ግንባታ መጀመር**” ማለት በቦታው ላይ ለመስራት ከተፈቀደው ግንባታ ወይም ህንጻ ቢያንስ የመሰረት ስራ መስራትና የኮለን ግንባታ ለማከናወን የሚያስችሉ የኮለን ብረቶች የማቆም ሥራ ማጠናቀቅ ነው፤

22) “**ግንባታ ማጠናቀቅ**” ማለት በሊዝ የተፈቀደ ቦታ ላይ እንዲገነባ የተፈቀደን ግንባታ በተሰጠው የግንባታ ፈቃድ መሠረት ሙሉ በሙሉ መስራትና ዋና ዋና አገልግሎቶች ተሟልተውለት ለአገልግሎት ዝግጁ ማድረግ ነው፤

23) “ሰው” ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

24) በዚህ መመሪያ በወንድ ፆታ የተገለፀው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ መመሪያ፡-

(1) በሥራና ስልጠና ተቋም ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ ተሸጋግረው ርክክብ የተደረገላቸው፣

(2) በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም የደረጃ ሽግግር አፈፃፀም መሠረት ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ተሸጋግረው የመስሪያ ቦታ/መሬት ለሚጠይቁ እና

(3) ወደ ክላስተር ማዕከላት ለመግባት ጥያቄ በሚያቀርቡ አነስተኛ እና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

ክፍል ሁለት

ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ እና ወደ ክላስተር ማዕከላት ለሚገቡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ ለማግኘት ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታ እና መመልመያ መስፈርት፤

4. ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፤ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ ለማግኘት ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች፤

(1) በደረጃ ሽግግር አፈጻጸም መመሪያ መሰረት ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፤ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ ለመሆኑ ማስረጃ ማቅረብ የሚችሉ፤

(2) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩና ያለቀለት የኢንዱስትሪ ምርት የሚያመርቱ ወይም ለሌላ ኢንዱስትሪ ግብዓት የሚሆኑ በከፊል ያለቀለት ምርት የሚያመርቱ፤

(3) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፤ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ ኢንዱስትሪዎች ወቅታዊና አዋጭ የሆነ የንግድ ሥራ ዕቅድ ወይም የፕሮጀክት ሀሳብ እና ሌይ አውት ማቅረብ የሚችሉ፤

(4) የዘመኑን ግብር በወቅቱ የከፈሉ ለመሆናቸው ማስረጃ የሚያቀርቡ፤

(5) መንግሥት በገነባው ሸድ ውስጥ እየሰሩ ያሉ ከሆኑ የሸድ ኪራይ ውዝፍ ዕዳ የሌለባቸው፣ በጊዜያዊነት የመስሪያ ቦታ የወሰዱ ከሆኑ ደግሞ የሊዝ ኪራይ ውዝፍ ዕዳ የሌለባቸው ለመሆኑ ማስረጃ የሚያቀርቡ፡፡

(6) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፤ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች በሚከተለው ሁኔታ በአራቱ ንዑስ ዘርፎች ይደራጃሉ፡-

ሀ) በጨርቃጨርቅ፣ ቆዳና አልባሳት ንዑስ ዘርፎች፤

ለ) በአግሮፕሮሰሲንግ፣ ምግብና ፋርማሲዮቲካል ንዑስ ዘርፎች፤

ሐ) በእንጨትና ብረታብረት ንዑስ ዘርፎች እና

መ) በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ንዑስ ዘርፎች፣

5. ወደ ክላስተር ማዕከላት የሚገቡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ማሟላት ያለባቸው ቅድመ ሁኔታዎች

(1) ለግምገማ የሚቀርበው የፕሮጀክት ሀሳብ ወይም የንግድ ስራ እቅድ አዋጭነቱ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳ ሊያሟላ በሚችል መልኩ መሆን ይኖርበታል፤

(2) የፕሮጀክቶች ማሽን ሌይ አውት (Machine layout) ማቅረብ አለባቸው፤

(3) በማስረጃነት የሚቀርበው ማሽን ሌይ አውት ከፕሮፎርማ ወይም ከማሽን አምራች ካንፓኒው የመረጃ መረብ የሚወሰድ ይሆናል፤

(4) አምራች ኢንዱስትሪዎች ነባር ከሆኑ የዘመኑን ግብር በወቅቱ የከፈሉ ለመሆናቸው ማስረጃ የሚያቀርቡ፤

(5) አምራች ኢንዱስትሪዎች መንግስት በገነባው ሽድ ውስጥ እየሰሩ ያሉ ከሆኑ የሽድ ኪራይ ውዝፍ ዕዳ የሌለባቸው፣ በጊዜያዊነት የመስሪያ ቦታ የወሰዱ ከሆኑ ደግሞ የሊዝ ኪራይ ውዝፍ ዕዳ የሌለባቸው ለመሆኑ ማስረጃ የሚያቀርቡ፤

(6) ወደ ክላስተር ማዕከላት የሚገቡአነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በሚከተለው ሁኔታ በአራቱ ንዑስ ዘርፎች ይደራጃሉ፡-

ሀ) በጨርቃጨርቅ፣ ቆዳና አልባሳት ንዑስ ዘርፎች፤

ለ) በአግሮፕሮሰሲንግ፣ ምግብና ፋርማሲዮቲካል ንዑስ ዘርፎች፤

ሐ) በእንጨትና ብረታ ብረት ንዑስ ዘርፎች፤

መ) በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ንዑስ ዘርፎች፡፡

6. ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ እና ወደ ክላስተር ማዕከላት ለሚገቡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ ለማግኘት የሚያስችል መመልመያ መስፈርት

ከላይ በአንቀፅ 4 እና 5 የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ የመስሪያ ቦታ/መሬት/ የሚሰጣቸው ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፤ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ እና ወደ ክላስተር ማዕከላት

የሚገቡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች በየንዑስ ዘርፋቸው እርስ በእርስ ተወዳድረው የነጥብ ክብደቱ እየታየ የሚመዘኑ ይሆናል፡፡ ይኸውም፡-

(1) ለውጭ ምርት ማምረት 10 ነጥብ

(2) ተኪ ምርት ማምረት ለሚችሉ 10 ነጥብ

(3) ለቴክኖሎጅ ፈጠራና አጠቃቀም 10 ነጥብ

(4) ለስራ ዕድል ፈጠራ 30 ነጥብ

(5) ለኢንቨስትመንት ካፒታል 25 ነጥብ

(6) የግብዓት አጠቃቀም 15 ነጥብ ይሰጣል

(1) ለወጭ ምርት ማምረት 10 ነጥብ

ምርቶቻቸውን ለውጭ ገበያ ለሚያቀርቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንደየንዑስ ዘርፋቸው ክብደት የሚያገኙ ሲሆን ውጤት የሚሰጣቸው በተጨባጭ ለወጭ ምርት የሚያቀርቡት 50 በመቶ እና በንግድ ስራ ዕቅዳቸው ወይም የፕሮጀክት ሀሳባቸው ላይ ያስቀመጡት የወጭ ምርት መጠን ደግሞ 50 በመቶ የሚያዝ ሆኖ የሁለቱ አማካይ ውጤት የመጨረሻ ውጤት ይሆናል፡፡

ሀ) በጨርቃጨርቅ፣ አልባሳትና የቆዳ ውጤቶች የተሰማሩ 60 በመቶና በላይ ወደ ውጭ ከላኩ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 50 በመቶና በላይ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ እንዲያገኙ ይደረጋል፤

ለ) በአግሮ-ፕሮሰሲንግ፣ ምግብና ፋርማሲዩቲካል ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ 50 በመቶና በላይ ወደ ውጭ ከላኩ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 40 በመቶ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ እንዲያገኙ ይደረጋል፤

ሐ) ኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት፣ እንጨትና ብረታብረት ንዑስ ዘርፎች የተሰማሩ 40 በመቶ ወደ ውጭ ከላኩ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 50 በመቶና በላይ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ ያገኛሉ፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር ከተዘረዘሩት የከፍተኛ ነጥብ በታች የሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ነጥብ የከፍተኛውን መነሻ በማድረግ በመቶኛ እየተሰላ የሚሰጥ ይሆናል፤

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ስር የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ሁለቱንም ተግባራት በአንድ ላይ የሚያከናውን አምራች ኢንዱስትሪ ከሆነ ስሌቱ በሁለቱም ተሰርቶ ይደመርና ከከፍተኛው ነጥብ ከበለጠ ከፍተኛውን ነጥብ ብቻ ይሰጠዋል፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ በጨርቃጨርቅ ንዑስ ዘርፍ የተሰማራ አምራች ኢንዱስትሪ በተግባራዊ ሂደቱ ሲመዘን ምንም ምርት ወደ ውጭ የማይልክ ከሆነ ዜሮ ነጥብ ይሰጠዋል፤

ነገር ግን ባቀረበው የንግድ ስራ ዕቅድ ወይም የፕሮጀክት ሀሳብ 30 በመቶ ምረቱን ወደ ውጭ የሚልክ መሆኑን ቢያሳይ (30/60)*10= 5 ይሆናል፡፡ ኢንዱስትሪው የሚያገኘው ጠቅላላ ውጤት (0 +5)/2 = 2.5 ነጥብ ይሰጠዋል ማለት ነው፤

ረ) በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚያቀርቡ ከሆነ በተመሳሳይ መንገድ የሚሰራ ይሆናል፡፡

(2) ተኪ ምርት ማምረት ለሚችሉ 10 ነጥብ

ተኪ ምርት ማምረት የሚችሉ አምራች ኢንዱስትሪዎች እንደየንዑስ ዘርፋቸው ክብደት የሚያገኙ ሲሆን ውጤት የሚሰጣቸው በተጨባጭ ገቢ ምርትን መተካት የሚችሉ 50 በመቶ እና በንግድ ስራ ዕቅዳቸው ወይም የፕሮጀክት ሀሳባቸው ላይ ያስቀመጡት የተኪ ምርት መጠን ደግሞ 50 በመቶ የሚያዝ ሆኖ የሁለቱ አማካይ ውጤት የመጨረሻ ውጤት ይሆናል፤

ሀ) በብረታ ብረት እና እንጨት ውጤቶች የተሰማሩ 60 በመቶና በላይ ተኪ ምርት የሚያመርቱ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 50 በመቶና በላይ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ እንዲያገኙ ይደረጋል፤

ለ) በኬሚካልና ኮንስትራክሽን ግብዓት ንዑስ ዘርፎች የተሰማሩ 50 በመቶና በላይ ተኪ ምርት የሚያመርቱ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 50 በመቶና በላይ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ ያገኛሉ፤

ሐ) በጨርቃጨርቅ፣ አልባሳትና የቆዳ ውጤቶች የተሰማሩ 40 በመቶና በላይ ተኪ ምርት የሚያመርቱ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 50 በመቶና በላይ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ እንዲያገኙ ይደረጋል፤

መ) በአግሮፕሮሰሲንግ፣ ምግብና ፋርማሲዩቲካል ንዑስ ዘርፍ የተሰማሩ 30 በመቶና በላይ ተኪ ምርት የሚያመርቱ ወይም በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት 50 በመቶና በላይ የሚያቀርቡ ከሆነ 10 ነጥብ እንዲያገኙ ይደረጋል፤

ሠ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር ከተዘረዘሩት ከከፍተኛ ነጥብ በታች ተኪ ምርት የሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጠው ነጥብ የከፍተኛውን መነሻ በማድረግ በመቶኛ እየተሰላ የሚሰጥ ይሆናል፤

ረ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ስር የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ሁለቱንም ተግባራት በአንድ ላይ የሚያከናውን አምራች ኢንዱስትሪ ከሆነ ስሌቱ በሁለቱም ተሰርቶ ይደመርና ከከፍተኛው ነጥብ ከበለጠ ከፍተኛውን ነጥብ ብቻ ይሰጠዋል፡፡

ለምሳሌ፡- አንድ በጨርቃጨርቅ ንዑስ ዘርፍ የተሰማራ አምራች ኢንዱስትሪ በተግባራዊ ሂደቱ ሲመዘን ምንም ተኪ ምርት የማያመርት ከሆነ ዜሮ ነጥብ ይሰጠዋል፡፡ ነገር ግን ባቀረበው የንግድ ስራ ዕቅድ ወይም የፕሮጀክት ሀሳብ 30 በመቶ ምረቱን ገቢ ምርትን የሚተካ መሆኑን ቢያሳይ (30/40)*10= 7.5 ይሆናል፡፡ ኢንዱስትሪው የሚያገኘው ጠቅላላ ውጤት (0 +7.5)/2 = 3.75 ነጥብ ይሰጠዋል ማለት ነው፤

ሰ) በከፊል ያለቀለት ምርት አምርተው ተኪ ምርት ለሚያመርቱ አምራች ኢንዱስትሪዎች በግብዓትነት የሚያቀርቡ ከሆነ በተመሳሳይ መንገድ የሚሰራ ይሆናል፤

(3) ለቴክኖሎጅ ፈጠራና አጠቃቀም 10 ነጥብ

አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያቀርቡት ቴክኖሎጅ ውጤት የሚያሰጣቸው በተጨባጭ አዲስ ቴክኖሎጂ ለፈጠረ ወይም ለተጠቀመ 50 በመቶ እና በንግድ ስራ ዕቅዳቸው ወይም በፕሮጀክት ሀሳባቸው ላይ ያስቀመጡትን ቴክኖሎጂ ፈጠራና አጠቃቀም ደግሞ 50 በመቶ የሚያዝ ሆኖ የሁለቱ አማካይ ውጤት የመጨረሻ ውጤት ይሆናል፤

ሀ) በተጨባጭ ሥራ ላይ የሚታዩ ነጥቦች፡-

1. ለሀገራችን አዲስ የሆነ 3 ነጥብ፤
2. አዲስ ባይሆንም ቴክኖሎጂው ምርትን በተሻለ ጥራትና ፍጥነት ለማምረት የሚያስችል ከሆነ 2 ነጥብ፤
3. የማምረት አቅሙ ከፍተኛ ከሆነ 3 ነጥብ፤
4. የሚጠቀመው ሃይል መጠን አነስተኛ ከሆነ 1 ነጥብ፤
5. ከአካባቢው ባሕልና እሴት ጋር የማይቀረን ከሆነ 1 ነጥብ፤

ለ) በንግድ ሥራ ዕቅዱ ወይም በፕሮጀክት ሀሳቡ ላይ የሚታዩ ነጥቦች፡-

1. ለሀገራችን አዲስ የሆነ 3 ነጥብ፤
2. አዲስ ባይሆንም ቴክኖሎጂው ምርትን በተሻለ ጥራት፣ መጠን ለማምረት በአሰራር የተሻለ ከሆነ 2 ነጥብ፤
3. የማምረት አቅሙ ከፍተኛ ከሆነ 3 ነጥብ፤
4. የሚጠቀመው ሃይል መጠን አነስተኛ ከሆነ 1 ነጥብ፤

5. ከአካባቢው ባሕልና እሴት ጋር የማይቀረን ከሆነ 1 ነጥብ፤

(4) **ለሥራ ዕድል ፈጠራ 30 ነጥብ**

አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚፈጥሩት ቋሚ የሥራ ዕድል ውጤት የሚያሰጣቸው በተጨባጭ የፈጠሩት የሥራ ዕድል መረጃ 50 በመቶ እና በንግድ ሥራ ዕቅዳቸው ወይም በፕሮጀክት ሃሳባቸው ላይ ያስቀመጡትን መረጃ ደግሞ 50 በመቶ የሚያዝ ሆኖ የሁለቱ አማካይ ውጤት የመጨረሻ ውጤት ይሆናል፡፡ ነገር ግን በተጨባጭ የፈጠሩትን የሥራ ዕድል የሚያሳይ የመጨረሻዎቹን ስድስት ወራት ፔሮልና ለሠራተኞች የገቢ ግብር የተከፈለበትን ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ ወደ ክላስተር ማዕከላት ለመግባት ጥያቄ የሚያቀርቡ አዳዲስ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከሆኑ የንግድ ሥራ ዕቅዳቸው/ፕሮጅክት ሀሳባቸው ላይ የተቀመጠውን የትርጉሙን መዳረሻ ማሟላታቸውን በማየት የሚወዳደሩ ይሆናል፡፡ **ስለሆነም፡-**

ሀ) ለግምገማ የቀረበው ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ የተሸጋገረ አምራች ኢንዱስትሪ 50 እና በላይ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገረ አምራች ኢንዱስትሪ ደግሞ 100 እና በላይ ለሆኑ ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል የፈጠር ከሆነ 30 ነጥብ ያገኛል፤

ለ) ለግምገማ የቀረበው ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ የተሸጋገረ አምራች ኢንዱስትሪ ከ50 በታች፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገረ አምራች ኢንዱስትሪ ደግሞ ከ100 በታች ለሚሆኑ ዜጎች ቋሚ የስራ ዕድል የፈጠረ ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድርግ በስሌት የሚሰራ ይሆናል፤

ሐ) ይሁን እንጅ በሁለቱም መመዘኛዎች ከትርጉሙ መነሻ በታች የሰው ኃይል ያለው ከሆነ ነጥብ አያገኝም፡፡

(5) **ለኢንቨስትመንት ካፒታል 25 ነጥብ**

አምራች ኢንዱስትሪዎች ያፈሩት የኢንቨስትመንት ካፒታል ውጤት የሚያሰጣቸው በተጨባጭ ያፈሩት የኢንቨስትመንት ካፒታል መጠን 50 በመቶ እና በንግድ ሥራ ዕቅዳቸው ወይም በፕሮጀክት ሃሳባቸው ላይ ያስቀመጡት ካፒታል ደግሞ 50 በመቶ የሚያዝ ሆኖ የሁለቱ አማካይ ውጤት የመጨረሻ ውጤት ይሆናል፡፡ ነገር ግን በተጨባጭ ያፈሩትን የኢንቨስትመንት ካፒታል ትክክለኛነት የሚያሳይ የፋይናንሻል ኦዲት ሪፖርት ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅባቸዋል፡፡ ይሁን እንጅ ወደ ክላስተር ማዕከላት ለመግባት ጥያቄ የሚያቀርቡ አዳዲስ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከሆኑ የንግድ ሥራ ዕቅዳቸው /ፕሮጅክት/ ሀሳባቸው ላይ የተቀመጠውን የኢንቨስትመንት ካፒታል መጠን የትርጉሙን መዳረሻ ማሟላታቸውን በማየት የሚወዳደሩ ይሆናል፡፡ **ስለሆነም፡-**

ሀ) ለግምገማ የቀረበው ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ የተሸጋገረ አምራች ኢንዱስትሪ 600,001 ብር እና በላይ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገረ አምራች ኢንዱስትሪ ደግሞ 90 ሚሊዮን ብር እና በላይ ሀብት ያለው ከሆነ 25 ነጥብ ያገኛል፤

ለ) ለግምገማ የቀረበው ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ የተሸጋገረ አምራች ኢንዱስትሪ ከ600,001 ብር በታች፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገረ አምራች ኢንዱስትሪ ደግሞ ከ90 ሚሊዮን ብር በታች ከሆነ የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድርግ በስሌት የሚሰራ ይሆናል፤

ሐ) ይሁን እንጅ በሁለቱም መመዘኛዎች ከትርጉሙ መነሻ በታች የኢንቨስትመንት ካፒታል መጠን ያለው ከሆነ ነጥብ አያገኝም፡፡

(6) የጥሬ ዕቃ አጠቃቀም 15 ነጥብ

ሀ) የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ወይም በከፊል ያለቀለት የሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ምርቶችን 80 በመቶና በላይ የሚጠቀሙ አምራች ኢንዱስትሪዎች 15 ነጥብ ያገኛሉ፤

ለ) የሀገር ውስጥ ጥሬ ዕቃ ወይም በከፊል ያለቀለት የሀገር ውስጥ የኢንዱስትሪ ምርቶችን ከ80 በመቶ በታች የሚጠቀሙ አምራች ኢንዱስትሪዎች የከፍተኛውን ነጥብ መነሻ በማድረግ በስሌት ይሰራል፤

ሐ) የአምራች ኢንዱስትሪው የሚጠቀመውን የጥሬ ዕቃ ሙሉ በሙሉ ከውጭ አገር አስመጥቶ የሚጠቀም ከሆነ የከብደቱን 25 በመቶ ነጥብ ይሰጠዋል፤

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ ሐ) የተጠቀሰው ለነባር አምራች ኢንዱስትሪዎች ውጤት የሚሰጠው በተግባር ላይ ያለውን የግብዓት አጠቃቀም መረጃ በመውሰድ ሲሆን ለአዳዲሶች ግን የንግድ ስራ ዕቅዱ/ፕሮጀክት ሰነዱ ላይ የተቀመጠውን በማየት የሚሰጥ ይሆናል፡፡

ሠ) በበዚህ አንቀጽ የተጠቀሱት እንደተጠበቁ ሆነው በማህበር ለተደራጁ የሴቶች ቁጥር ከ25-49 በመቶ ከሆነ ተጨማሪ 3 ነጥብ ለማበረታቻነት ይሰጣል፡፡

ረ) በሴቶች ባለቤትነት ወይም በማህበር ለተደራጁ የሴቶች ቁጥር 50 በመቶና በላይ ከሆነ እንደሴቶች ባለቤትነት ተቆጥሮ ተጨማሪ 5 ነጥብ ለማበረታቻነት ይሰጣል፡፡

ሸ) በአንቀጽ 6 ንዑስ አንቀጽ (6) የተዘረዘሩት እደተጠበቁ ሆነው እኩል ነጥብ ሲያስመዘግቡ፡-

1. ውድድሩ በወንድና በሴት መካከል ከሆነ ቅድሚያ ለሴት ይሠጣል፡፡
2. ውድድሩ በግለሰብና በማህበር (በንግድና በህብረት ሥራ ማህበር) ከሆነ ቅድሚያ ለማህበር ይሰጣል፡፡
3. ውድድሩ በተመሳሳይ ጾታና አደረጃጀት ከሆነ ባለው ኢኮኖሚያዊ ፋይዳ ይመረጣል፡፡

ክፍል ሦስት
የመስሪያ ቦታ ዝግጅት፣ የማለፊያ ነጥብ አሰጣጥ እና የመስሪያ ቦታ መጠን አወሳሰን

7. የመስሪያ ቦታ ዝግጅት፤

(1) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ ለማግኘት ከከፍተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ጋር የመወዳደር አቅም ስለማይኖራቸው ከተማው ወይም ወረዳ አስተዳደሩ በየንዑስ ዘርፋቸው እርስ በእርስ በአንቀጽ 6 ስር በተዘረዘሩት መስፈርቶች መሰረት በማወዳደር አሸናፊ ለሚሆኑት የመስሪያ ቦታ ማዘጋጀት፣ ማልማትና ማስተላለፍ ሥራ ይሰራል፤

(2) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለሚሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚሰጥ ቦታ ዝግጅት ከከተማው የወደፊት እድገት ጋር የሚጣጣም፣ ሁሉን አቀፍ የተቀናጀ ድጋፍ ለመስጠት የሚያስችል፣ እንዲሁም ውጤታማና ቀልጣፋ የመሰረተ-ልማት አገልግሎች ለመዘርጋት የሚያመች ሆኖ መደራጀት አለበት፤

(3) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለሚሸጋገሩ አምራች ኢንደስትሪዎች የተለዩ ቦታዎች የከተማ ወይም የወረዳ አስተዳደሩ ያዘጋጀውን መሬት በሚመለከተው ተቋም የካሳ ክፍያ ተመን በመስራት ትክክለኛነቱን አረጋግጦ ሲያቀርብ ባለሀብቱ የካሳ ክፍያውን እንዲከፈል በማድረግ ከሶስተኛ ወገን ነፃ እንዲሆንና መሰረተ-ልማቱ እንዲሟላለት እያደረገ ተወዳድረው ለሚያሸንፉ ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ አምራች ኢንደስትሪዎች ያስተላልፋል፤

(4) መንግሥት በራሱ በጀት ለአነስተኛ እና መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚዘጋጁ ክላስተር ማዕከላት ሊገነቡባቸው የሚችሉ የመስሪያ ቦታዎችን በመለየት እና ከዚህ በፊት በመንግሥት የተገነቡ ክላስተር ማዕከላትን ችግሮቻቸውን እየፈቱ ለመስሪያ ምቹ በማድረግ ወደ ክላስተር ማዕከላት ለመግባት በጥያቄው መሠረት ተወዳድረው ላለፉ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ያስተላልፋል፡፡

8. የማለፊያ ነጥብ አሰጣጥ

(1) የመስሪያ ቦታ የሚሰጣቸው ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ እና ወደ ክላስተር ማዕከላት የሚገቡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ከላይ የተቀመጡትን የማወዳደሪያ ነጥቦች እንደቅደም ተከተላቸው በሚያመጡት ውጤት መሰረት እየታየ ባለው የመሬት አቅርቦት መጠን ወይም የክላስተር አይነት የሚሰጥ ይሆናል፤

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) የተገለፀው እንደተጠበቀ ሆኖ ውድድሩ የደረጃ ሽግግር ባደረጉት እና የንግድ ስራ እቅድ/የፕሮጀክት/ ሀሳብ ብቻ በሚያቀርቡት አምራች ኢንዱስትሪዎች መካከል ከሆነ የደረጃ ሽግግር ላደረጉት አምራች ኢንዱስትሪዎች ቅድሚያ የሚሰጥ ይሆናል፡፡

9. የመስሪያ ቦታ መጠን አወሳሰን፤

(1) ለግምገማ የሚቀርበው የአምራች ኢንዱስትሪ የንግድ ስራ እቅድ ወይም የፕሮጀክት ሀሳብ አዋጭነቱ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ፋይዳው ታይቶ የተሻለና ቅድመ ሁኔታዎችን ያሟላ ሆኖ ሲገኝ ለውድድር ይመለመላል፤

(2) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገረ እና ወደ ክላስተር ማዕከላት ለሚገቡ አነስተኛ ወይም መካከለኛ አምራች ኢንዱስትሪ የሚሰጠው የቦታ መጠን የሚወሰነው ባለሃብቱ በሚያቀርበው ፕላንትና ማሽን ሌይ አውት መሰረት ይሆናል፤

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ለተጠቀሰው በማስረጃነት የሚቀርበው ማሽን ሌይ አውት ኢንዱስትሪው የሚሰራባቸውን ማሽኖችና ተጨማሪ ተገዝተው የገቡ ማሽኖች ሲኖሩ ደግሞ ማሽኖቹ የተገዙበትን ደረሰኝ (Commercial Invoice)፣ በንግድ ስራ ዕቅዱ መሠረት ተገዝተው ለሚገቡ ማሽነሪዎች ደግሞ ከአምራቾችና አቅራቢዎች ማስረጃ ማቅረብ ይጠበቅበታል፤

(4) ለፕላንት ሌይ አውቱ ደግሞ በስታንዳርዱ መሰረት ገምጋሚ ኮሚቴው ከሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ በመነሳት በየደረጃው የሚገኘው ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም የማኔጅመንት አካል የሚወሰን ይሆናል፡፡

ክፍል አራት
ውጤትን ይፋ ስለማድረግ፣ የመስሪያ ቦታ /መሬት/ ስለማስተላለፍ እና ወደ ትግበራ ስለማስገባት

10. ውጤትን ይፋ ስለማድረግ

(1) ለቀረበው ንግድ ስራ ዕቅድ/ፕሮጀክት የሚያስፈልገው የመሬት መጠን ወይም ክላስተር ማዕከል በተቋሙ ገምጋሚ ኮሚቴ ተገምግሞ በማኔጅመንት ከፀደቀ በኂላ ለከተማ ከንቲባ/ምክትል ከንቲባ ወይም ለወረዳ ዋና አስተዳዳሪ/ምክትል አስተዳዳሪ ወይም በእነዚህ አካላት ህጋዊ ውክልና የተሰጠው አካል እንዲያፀድቀው በማድረግ ቢሮዉ የፀደቀውን ውጤት በ3 ቀናት ውስጥ ይፋ ያደርጋል፤

(2) ውጤቱ ይፋ ከሆነበት ቀን ጀምሮ በማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ ለ5 ተከታታይ የስራ ቀናት የሚቆይ ይሆናል፤

(3) ቢሮዉ በማስታወቂያ ከገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ ምንም ቅሬታ ካልቀረበ የተወሰነለትን የመሬት መጠን ወይም የመስሪያ ቦታ ለባለሀብቱ ያስተላልፋል፡፡

11. የመስሪያ ቦታ ወይም መሬት ማስተላለፍ እና ወደ ትግበራ ማስገባት

(1) በአንቀጽ 6 በተገለጹት የመመልመያ መስፈርቶች መሰረት ተገምግሞ ላለፈ ንግድ ስራ ዕቅድ ወይም ፕሮጀክት መሬት/መስሪያ ቦታ የተላለፋል፤

(2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሰረት የተሰጠዉን መሬት ከሚመለከተዉ ተቋም የሊዝ ዉል በመዉሰድ ካርታና ፕላን በስሙ በማሰራት በ1ወር ጊዜ ዉስጥ እንዲያጠናቅቅ ማድረግ፤ ክላስተር ማዕከል ከሆነ ደግሞ ከሚመለከተው ተቋም የኪራይ ውል በአንድ ወር ውስጥ በመውሰድ ወደ ተግባር እንዲገባ ማድረግ፤

(3) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) ካርታና ፕላን የተሰራለት ፕሮጀክት በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት የተሻሻለዉ የከተማ ቦታን በሊዝ ለማስተዳደር የወጣዉ ደንብ ቁጥር 103/2004 አንቀጽ 36 ንኡስ አንቀጽ (1) መሰረት ከ9 ወር ባልበለጠ ጊዜ ዉስጥ የግንባታ ፈቃድ እንዲያወጣ ይደረጋል፤

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የግንባታ ፈቃድ የተሰጠዉ ፕሮጀክት የሊዝ ዉል ከወሰደበት ጊዜ ጀምሮ ለመካከለኛ ግንባታ 12 ወራት፤ ለከፍተኛ ግንባታ በ18 ወራት ዉስጥ ግንባታዉን እንዲጀምር ይደረጋል፤

(5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) የግንባታ ፈቃድ የተሰጠዉ ፕሮጀክት ግንባታ ለማጠናቀቅ ለመካከለኛ ግንባታ 24 ወር /ሁለት አመት/፤ ለከፍተኛ ግንባታ 36 ወር /3 አመት/ ግንባታዉን እንዲያጠናቅቅ የሚደረግ ሆኖ ግንባታዉን በዉቅቱ ያላጠናቀቀዉ ከአቅም በላይ በሆኑ ምክንያቶች መሆኑን ቢሮው በማስረጃ ሲያረጋግጥ ተጨማሪ የአንድ አመት ጌዜ ተሰጥቶት እንዲያጠናቅቅ ይደረጋል፡፡

(6) በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (1) እስከ (5) የተዘረዘሩት እንደተጠበቁ ሆነው ግንባታውን በተቀመጠለት የጊዜ ገደብ ውስጥ በማጠናቀቅ ምርት ወደ ማምረት እንዲገባ ይደረጋል፡፡

ክፍል አምስት
መሬት/የመስሪያ ቦታ/ ወስደው በውላቸው መሠረት ወደ ትግበራ በማይገቡ ባለሀብቶች ላይ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች እና ቅሬታን ስለማስተናገድ

12. **መሬት/የመስሪያ ቦታ/ ወስደው በውላቸው መሠረት ወደ ትግበራ በማይገቡ ባለሀብቶች ላይ ስለሚወሰዱ እርምጃዎች፡-**

(1) ቢሮው መሬት /መስሪያ ቦታ የሰጣቸውን የአምራች ኢንዱስትሪ የንግድ ሥራ ዕቅድ/ የፕሮጀክቶች ሰነዱን ሙሉ መረጃ አደራጅቶ በመያዝ ለድጋፍና ክትትል ምቹ ሁኔታ እንዲፈጠር ያደርጋል፤

(2) በአንቀጽ 11 ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ (5) የተገለጹትን የግንባታ ደረጃዎችን ሂደት ድጋፍና ክትትል ማድረግ፤

(3) በአንቀጽ 11 ከንዑስ አንቀጽ (2) እስከ (5) በተገለጹት የግንባታ ጊዜ ገደብ መሰረት ወደ አፈጻጸም ያልገቡ ፕሮጀክቶችን፡-

ሀ) የግንባታ ጊዜው ከማለቁ በፊት አንድ ወር ቀደም ብሎ የፕሮጀክቱን ባለቤት ወይም ህጋዊ ወኪልና ለተሰጠዉ አካል ቢሮው የቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጠዋል፤

ለ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ ሀ) መሰረት የተሰጠዉን የቃል ማስጠንቀቂያ ተግባራዊ ካላደረገ የግንባታ ጊዜው በተጠናቀቀ በሦስተኛው ወር መጨረሻ ላይ ቢሮው የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ደብዳቤ በአድራሻው ወይም በአካባቢዉ በሚገኝ የህዝብ ማስታወቂያ ሰሌዳ ላይ በመለጠፍ ግዴታዉን እንዲያዉቀዉ ያደረጋል፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ፊደል ተራ ለ) መሰረት የተሰጠዉን የጹሁፍ ማስጠንቀቂያ ተግባራዊ ካላደረገ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ በተሰጠው በ3ኛው ወር መጨረሻ ላይ ቢሮው የተሰጠዉን ካርታ እንዲመክንና መሬቱም ወደ መሬት ባንክ እንዲገባ በማድረግ ለሚመለከተዉ ተቋም የማሳወቅ ስራ በመስራት ለሌላ አልሚ ባለሃብት እንዲተላለፍ ያደረጋል፤

(4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) ከፊደል ተራ ሀ) እስከ ሐ) የተገለጸዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ባለሃብቱ በተሰጠዉ መሬት ላይ ግንባታ ጀምሮ ያቋረጠ (ያላጠናቀቀ)፤ ግንባታ ሙሉ በሙሉ ያጠናቀቀና ማሽን አስገብቶ በወቅቱ ወደ ማምረት ያልገባ፤ እንዲሁም ምርት ጀምሮ ያለበቂ ምክንያት ያቋረጠ ከሆነ ከመሬት በላይ ያለዉን የንብረት ግምት በሚመለከተዉ ተቋም ተሰርቶ አዲስ የሚገባዉ ባለሃብት ግምቱን እንዲፈጽም

በማድረግ የሚተላለፍ ሲሆን መሬቱን ተረክቦ ባለማልማቱ ለመንግስትና ለህዝብ ያሳጣዉን ጥቅም ታሳቢ በማድረግ 10 ፐርሰንት ቅጣት እንዲከፍል የሚደረግ ይሆናል፤

(5) ወደ ክላስተር ማዕከላት በኪራይ የገቡ አምራች ኢንዱስትሪዎች በኪራይ ውላቸው መሠረት ወደ ስራ ካልገቡ በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም የክትትልና ድጋፍ ማስረጃን መሠረት ውል የያዘው አካል እርምጃ ይወስዳል፣ ውሳኔውንም ለቢሮው ያሳውቃል፡፡

13. ቅሬታን ስለማስተናገድ

(1) በንግድሥራ ዕቅድ/ፕሮጀክቶች/ ምልመላ ላይ የሚነሳን ቅሬታ ስለማስተናገድ፡-

ሀ) በዘርፉ መሰማራት የሚፈልግ የአምራች ኢንዱስትሪ የሚቀርብ ንግድ ሥራ ዕቅድ/ፕሮጀክቶች ሰነድ በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም ማለትም በወረዳ፣ በከተማ አስተዳደር እና በሪጅዮ-ፖሊታን ከተሞች እየቀረቡ የሚገመገሙ ሲሆን በግምገማ ሂደቱ ላይ ያልረካ አካል ሲኖር በየደረጃው /ቀጥሎ/ ባለው የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም እየታዩ ውሳኔ የሚሰጥ ይሆናል፤

ለ) በአንቀጽ 10 በተገለጸው መሠረት ውጤቱ በማስታወቂያ ከተገለጸበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ በኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም ዉሳኔ ያልረካ አካል ካለ ቅሬታውን ቀጥሎ ላለው የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም ማቅረብ ይችላል፤ ቅሬታው የቀረበለት ተቋምም ቅሬታው በቀረበ በሰባት /7/ ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ቅሬታዉን አይቶ ዉሳኔ ይሰጣል፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ፊደል ተራ ለ) ውሳኔ ያልረካ አካል ካለ ቅሬታውን በ7 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ለክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ማቅረብ ይችላል፤ ቅሬታ የቀረበለት የክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ቅሬታው በቀረበ 15 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ ይሰጣል፡፡ የክልሉ ኢንዱስትሪና ኢንቨስተመንት ቢሮ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

(2) የተነጠቀ መሬት/ቦታን አስመልክቶ ቅሬታን ስለማስተናገድ

ሀ) በአንቀጽ 12 ከንዑስ አንቀጽ (3) እስከ (5) በተገለጸዉ መሰረት በወረዳ /ከተማ አስተዳደር ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ጽሕፈት ቤት እርምጃ የተወሰደበት ፕሮጀክት /ባለሃብት/ ቅሬታ ካለዉ መሬቱ /ቦታዉ መነጠቁን በደብዳቤ ወይም በማስታወቂያ እንዲያዉቀዉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ የሥራ

ቀናት ዉስጥ ቅሬታዉን ለወረዳ አስተዳዳሪ/ም/አስተዳዳሪ ወይም ከተማ አስተዳደር ከንቲባ/ም/ከንቲባ ወይም በእነዚህ አካላት ህጋዊ ውክልና ለተሰጠው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታ የቀረበለት የወረዳ አስተዳዳሪ/ም/አስተዳዳሪ ወይም የከተማ አስተዳደር ከንቲባ/ም/ከንቲባ ቅሬታዉን አይቶ በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፤

ለ) በወረዳ አስተዳዳሪ ወይም ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ዉሳኔ ያልረካ አካል ቅሬታዉን ለዞን ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ በ7 ተከታታይ የሥራ ቀናት ውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታ የቀረበለት የዞን ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያም ቅሬታዉን አይቶ በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፤

ሐ) በዞን ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ ዉሳኔ ያልረካ አካል ካለ ቅሬታዉን ለዞን አስተዳዳሪ/ም/አስተዳዳሪ ወይም በዚህ አካል ህጋዊ ውክልና ለተሰጠው አካል በ7 ተከታታይ የስራ ቀናት ዉስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታ የቀረበለት የዞን አስተዳዳሪም/ም/አስተዳዳሪም ቅሬታዉን አይቶ በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፤

መ) በሪጅዮ-ፖሊታን ከተማ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት መምሪያ እርምጃ የተወሰደበት ፕሮጀክት /ባለሃብት/ ከሆነና ቅሬታ ካለዉ መሬቱ/ቦታዉ መነጠቁን በደብዳቤ ወይም በማስታወቂያ እንዲያዉቀዉ ከተደረገበት ቀን ጀምሮ ባሉት 5 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ቅሬታዉን ለሪጅዮ-ፖሊታን ከተማ ከንቲባ/ ም/ከንቲባ ወይም በዚህ አካል ህጋዊ ውክልና ለተሰጠው አካል ማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታ የቀረበለት የሪጅዮ-ፖሊታን ከተማ ከንቲባም/ም/ከንቲባም ቅረታዉን አይቶ በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፡፡

ሠ) በዞን አስተዳዳሪ/ም/አስተዳዳሪ ወይም በሪጅዮ-ፖሊታን ከተማ ከንቲባ/ም/ከንቲባ ዉሳኔ ያልረካ አካል ካለ ቅሬታዉን ለክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡ ቅሬታ የቀረበለት የክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮም ቅሬታዉን አይቶ በ15 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ዉሳኔ ይሰጣል፡፡

ረ) በክልል ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ውሳኔ ያልረካ አካል ካለ ቅሬታውን በ10 ተከታታይ የሥራ ቀናት ዉስጥ ለክልል ኢንቨስትመንት ቦርድ ማቅረብ ይችላል፡፡

ክፍል ስድስት

የቢሮ ተግባርና ኀላፊነት፤ የገምጋሚው ኮሚቴው አደረጃጀት እና ተግባርና ኀላፊነት፤

14. በየደረጃው የሚገኝ የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም ተግባርና ኀላፊነት

(1) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልገውን የመስሪያ ቦታ መጠን ለመወሰን ከሥራው ባህርይ እና ከሚቀርበው ለይ አውት በመነሳት ገምጋሚ ኮሚቴ በዚህ መመሪያ መሰረት ይሰይማል፤

(2) አምራች ኢንዱስትሪው በሽግግር አፈፃፀም መመሪያው መሠረት ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ መሆኑንና ቦታ ቢሰጣቸው ግንባታ ገንብተው ወደ ሥራ የሚገቡና ውጤት ሊያመጡ የሚችሉ መሆኑን ያረጋግጣል፤

(3) ከኢንዱስትሪ መንደር ይዞታ ውጭ አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ-ልማቶች እንዲዘረጉና ምቹ ሁኔታዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፣ ይከታተላል፤ ይደግፋል፤

(4) ቢሮዉ አግባብ ካላቸው የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር በክልሉ ውስጥ በአምራች ዘርፉ ለሚሰማሩ አነስተኛ እና መካከለኛ ኢንዱስትሪዎች አገልግሎት ሊውሉ የሚችሉ ሁለገብ የኢንዱስትሪ ፓርክ፣ የክላስተር ማዕከላት እና ከክላስተር ማዕከላትና ከኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ ለሚገቡ የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች የሚያስፈልገውን መሬት/የመስሪያ ቦታ/ ከሦስተኛ ወገኖች ይዞታ ነፃ እንዲሆን ከሚመለከተው አካልጋር ይሠራል፤ የቦታ፣ ካርታና ፕላን በማሠራትም ሆነ እስከ መዳረሻቸው የሚዘልቅ መሠረተ-ልማት እንዲሟላላቸው ያደርጋል፤

(5) ለአምራች ኢንዱስትሪ መስፋፋት ዘላቂ ፋይዳ ያለው የአዋጭነት ጥናትና የፕሮጀክት ትግበራ፣ ክትትልና ድጋፍ ሥርዓት ቀርፆ ተግባራዊ ያደርጋል፤

(6) በገጠርም ሆነ በከተማ በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ በኩል የሚቀርቡለትን ፕሮጀክቶች ይቀበላል፣ ወደ ክላስተር ማእከላት፣ የሁለገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ ከሁለገብ ኢንዱስትሪ ፓርክ ውጭ ሊገቡ የሚችሉትን በአይነት ይለያል፤ የፕሮጀክቶችን ፕላንት ሌይ አውት ይገመግማል፤ የሚያስፈልጋቸውን የመሬት መጠን ይወስናል፤

(7) በሚመለከተው አካል ተለይቶ በተዘጋጀው የኢንዱስትሪ ቀጠና አምራች ኢንዱስትሪዎች እዲስፋፉ ይሠራል፤ የቀጠናዎቹ ወሰንና የአጠቃቀም ለውጥ በመሬት ተቋም እዲመዘገብ ያደርጋል፤

(8) ተለይቶ የተዘጋጀውን ወደየ ኢንዱስትሪ ቀጠና እንዲገቡ ለተመረጡ አልሚዎች ያቀረቧቸውን ፕሮጀክቶች በመገምገምና የመሬት መጠን በመወሰን ውል ይዞ መሬት ያስተላልፋል፤ እንዳስፈላጊነቱ የመሠረተ-ልማት ማሟላት ተግባራትን ያከናውናል፤

በውላቸው መሠረት በማያለሙት ላይ ሕጋዊ እርምጃ ይወስዳል፤ መሬቱን ተመላሽ በማድረግ ለክልል መሬት ቢሮ እና ለፌደራል ኢንቨስትመንት ኮሚሽን በማሳወቅ ለሌላ አልሚ ያስተላልፋል፤

(9) በክልሉ ውስጥ በኢንቨስትመንት ሥራ የተሰማሩ ባለሀብቶችን ያበረታታል፤ ይደግፋል፤ ፈጥነው ወደ አፈጻጸም በማይገቡ ፕሮጀክቶች ላይ ደግሞ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመተባበር ፈቃድ የመሰረዝና መሬት የማስመለስ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስዳል፤ እንዲወሰዱ ያደርጋል፤

(10) በፕሮጀክት ሐሳባቸው ቃል የገቡትን የቴክኖሎጅ ሽግግር፣ ካፒታል እና የሥራ እድል ተግባራዊ እንዲያደርጉ ይከታተላል፤ ተግባራዊ በማያደርጉት ላይ እርምጃ ይወስዳል፤

(11) ባለሀብቶች በዚህ መመሪያ ይዘት ላይ የሚኖራቸው ግንዛቤ ከጊዜ ወደ ጊዜእ ንዲዳብር ግንዛቤና ሥልጠና ይሠጣል፤

(12) አግባብነት ካላቸው የክልሉና የፌደራሉ መንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ለአምራች ኢንዱስትሪዎች መስፋፋት እንቅፋት የሚሆኑ ማነቆዎች ተለይተው እንዲፈቱ ያደርጋል፤

(13) የአምራች ኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ወደ ሥራ እንዲገቡ ከፋይናንስ ተቋማት ጋር በመተባበር የብድር አገልግሎት እንዲመቻችላቸው ያደርጋል፤

(14) በአምራች ኢንዱስትሪ ዘርፍ የተሰማሩ ፕሮጀክቶች ዘርፍ መቀየር አስገዳጅ ሆኖ ሲገኝ የዘርፍ ለውጥ ያደርጋል፡፡

15. የገምጋሚ ኮሚቴው አደረጃጀት

(1) **በክልል**

ሀ) የኢንዱስትሪ ዞንና አካባቢ እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር ------------- ሰብሳቢ፣

ለ) ከኢንዱስትሪ ዞንና አካባቢ እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት የኢንቨስትመት ፕሮጀክት ድጋፍ ክትትል ባለሙያ --- አባልና ፀሐፊ፣

ሐ) የሚመለከተው የኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር --------- አባል፣

መ) ከኢንዱስትሪ ዞንና አካባቢ እንክብካቤ ዳይሬክቶሬት ሲቪል መሀንዲስ -------- አባል፣

ሠ) ከኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የሚመለከተው ኢንዱስትሪ መሀንዲስ/ባለሙያ---- አባል፤

(2) **በዞኖች፣ ሪጅዮ ፖሊታን ከተሞች እና በወረዳ/ከተማ አስተዳደር**

ሀ) የኢንቨስትመንት ማስፋፊያና ኢንዱስትሪ ዞን ልማት ቡድን መሪ ------------ሰብሳቢ፣

ለ) የኢንቨስትመንት ፕሮጀክቶች ድጋፍና ክትትል ባለሙያ --------------አባልና ፀሐፊ፣

ሐ) የኢንዱስትሪ ልማት ቡድን መሪ--አባል፣

መ) ከኢንቨስትመንት ማስፋፊያና ኢንዱስትሪ ዞን ልማት ቡድን ሲቪል መሀንዲስ-አባል፣

ሠ) ከኢንዱስትሪ ልማት ዘርፍ የሚመለከተው ኢንዱስትሪ መሀንዲስ/ባለሙያ-----አባል፤

16. የገምጋሚ ኮሚቴ ተግባርና ኀላፊነት

(1) **የክልል**

ሀ) የንግድ ሥራ ዕቅድ ወይም የፕሮጀክት ሀሳብ ለመገምገም ኮሚቴ አባላት ያልተሟሉባቸውን ሪጅዮ-ፖሊታን ከተሞች በመለየት የባለሙያ ድጋፍ እንዲደረግ ያመቻቻል፣

ለ) በንግድ ሥራ ዕቅድ ወይም በፕሮጀክት ሀሳብ ግምገማ አሰራር ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በማየት የውሳኔ ሃሳብ ለተቋሙ ማኔጅመንት ያቀርባል፣

ሐ) ከግምገማ ውጤቱ በመነሳት ጉደለትና ጥንካሬዎችን በመቀመር ትምህርት እንዲወሰድ ያደርጋል፤

(2) **የዞን**

ሀ) የንግድ ሥራ ዕቅድ ወይም የፕሮጀክት ሀሳብ ለመገምገም መዋቅር የሌለባቸውን ወረዳዎች/ከተሞች በመለየት ፕሮጀክቶችን ይገመግማል፣ ይመዝናል፣ የመሬት አቅርቦት መጠንን ይወስናል፣ ለተቋሙ ማኔጅመንት ያቀርባል፣

ለ) የንግድ ሥራ ዕቅድ ወይም የፕሮጀክት ሀሳብ ለመገምገም የገምጋሚ ኮሚቴ አባላት ያልተሟሉባቸውን ወረዳዎች/ከተሞች በመለየት የባለሙያ ድጋፍ እንዲደረግ ያመቻቻል፣ ዞኑ የሚመለከተው ባለሙያ ከሌለው ከሌሎች ወረዳዎች ወይም ከተሞች ባለሙያ በመዋስ እንዲገመግሙ ያመቻቻል፣

ሐ) በወረዳዎች ወይም ከተሞች የንግድ ስራ ዕቅድ ወይም የፕሮጀክት ሀሳብግምገማና አሰራር ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በማየት የውሳኔ ሃሳብ ለተቋሙ ማኔጅመንት ያቀርባል፣

መ) ከግምገማ ውጤቱ በመነሳት ጉደለትና ጥንካሬዎችን በመቀመር ትምህርት እንዲወሰድ ያደርጋል፤

(3) **የሪጅዮ-ፖሊታን ከተማ፣ የወረዳ/ከተማ አስተዳደር**

ሀ) የንግድ ሥራ ዕቅድ ወይም የፕሮጀክት ሀሳብ በዚህ መገምገሚያ መስፈርት መሰረት ይገመግማል፣

ለ) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሻጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የሚያስፈልጋቸውን የመሬት መጠን ይወስናል፣ የውሳኔ ሃሳቡንም ለተቋሙ ማኔጅመንት ያቀርባል፣

ሐ) ወደ ክላስተር ማዕከላት የሚገቡትን የመስሪያ ቦታ መጠን ይወስናል፤ ያስተላልፋል፤

መ) ከግምገማ ውጤቱ በመነሳት ጉደለትና ጥንካሬዎችን በመቀመር ትምህርት እንዲወሰድ ያደርጋል፤

ክፍል ሰባት
ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

17. ግዴታዎች

(1) ባለሃብቱ መሬቱን ከተረከበ በኋላ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም ለመከታተል፣ ለመደገፍና ለመቆጣጠር ለሚሰማሩ የተቋሙ ኃላፊዎችና ባለሙያዎች የሚያስፈልጉ ማናቸውንም መረጃዎች የመስጠት፣

(2) የአምራች ኢንዱስትሪ ባለሀብት የመስሪያ ቦታውን ወይም መሬቱን ከተረከበ በኋላ የፕሮጀክቱን አፈፃፀም በግንባታ ዕቅዱ መሰረት በየሶስት ወሩ ሳይቆራረጥ በየደረጃው ለሚገኙ የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም ሪፖርት ማድረግ አለበት፤

(3) በአንቀጽ 6 ስር በተዘረዘሩት መመልመያ መስፈርቶች መሰረት ተወዳድረው መሬት የተሰጣቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች በገቡት ውል መሰረት የመፈፀም ግዴታ አለባቸው፣ ያልፈፀሙ ባለሃብቶች የወሰዱትን የመስሪያ ቦታ ለመንግስት የሚመልሱ ይሆናል፤

(4) ከጥቃቅን ወደ አነስተኛ፣ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች ባቀረቡት ጥያቄ መሰረት ቦታ ከተረከቡና የግንባታ ፈቃድ ከወሰዱ በኋላ በፀደቀው የግንባታ ዝርዝርና ዲዛይን መሰረት መገንባት አለባቸው፤

(5) የመስሪያ ቦታ የሚሰጣቸው አምራች ኢንዱስትሪዎች ለሚወስዱት ቦታ በሊዝ አዋጁ የተቀመጠውን መነሻ የሊዝ ኪራይ ወይም በኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን መመሪያ መሰረት ኪራይ መክፈል ይጠበቅባቸዋል፤

(6) አምራች ኢንዱስትሪዎች በአዲስ ከሚቀበሉት መሬት/የመስሪያ ቦታ ላይ ግንባታ አጠናቀው ምርት ማምረት ሲጀምሩ ከዚህ በፊት በመንግስት የተሰጣቸው የመስሪያ ቦታ ካለ መመለስ ይጠበቅባቸዋል፤

(7) ምርታቸውን ወደ ውጭ አገር እንደሚልኩ ውል ገብተው ቦታ የተረከቡ ባለሀብቶች ወይም ምርታቸውን ወደ ውጭ ለሚልኩ ፋብሪካዎች በግብዓትነት የሚያቀርቡ ከሆነ፤ በገቡት ውል መሰረት እየፈጸሙ ስለመሆናቸው ምርት በጀመሩበት ዓመት መጨረሻ ጀምሮ በገቡት ውል መሰረት በየዓመቱ የግዥና ሽያጭ ውልና ደረሰኝ ማረጋገጫ በየደረጃው ለሚገኝ ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም ማቅረብ አለባቸው፤

(8) መሬት የተሰጠው ባለሀብት የግንባታ ፈቃድ ከማግኘቱ በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ (EIA) ማረጋገጫ ማቅረብ ይኖርበታል:: እንዲሁም ባለሃብቶች በአካባቢ ተጽዕኖ ግምገማ (EIA) መሰረት ያመላከታቸውን የአካባቢ ተጽዕኖንለመከላከል የሚያስችሉ ቴክኖሎጅዎችን ከፕሮጀክቱ ግንባታ ጎን ለጎን መፈጸም አለበት፤

(9) የመሬት ካሳ ከፍለዉ የሚገቡ ፕሮጀክቶች የከፈሉት የመሬት ካሳ ገንዘብ የሊዝ ክፍያዉን የሚሸፍን ሆኖ እስከተገኘ ድረስ የሊዝ ክፍያ ሳይጠየቁ የሚስተናገዱ ይሆናል፤

(10) መንግስት የመሬት ካሳ ከፍሎ ባዘጋጀው የመስሪያ ቦታ/መሬት ላይ የገቡ ባለሀብቶች በገቡት ውል መሰረት ወደ አፈፃፀም ካልገቡ ቦታው/መሬቱ ተነጥቆ ወደ መሬት ባንክ እንዲገባና ለሌላ ባለሀብት እንዲተላለፍ ሲደረግ ቦታው የሚተላለፍለት ባለሀብት የመሬት ካሳውን ወቅታዊ ግምት ከፍሎ የሚወስድ ይሆናል፡፡ ይሁን እንጅ በግለሰብ የተከፈለ የመሬት ካሳ ከሆነ፤ መሬቱ ተነጥቆ በሚተላለፍበት ጊዜ የሚተላለፍለት ባለሀብት ለተነጠቀው ባለሀብት የሚከፍለው የመሬት ካሳ የተነጠቀው ባለሀብት ቀደም ሲል የከፈለውን ካሳ ብቻ ይሆናል፤

(11) ወደ ክላስተር ማዕከላት ተመልምለው የሚገቡት አነስተኛ ወይም መካከለኛ የአምራች ኢንዱስትሪዎች ከዚህ በፊት በአምራች ኢንዱስትሪው ዘርፍ ስራ ያልጀመሩ ከሆኑ የአቅም ማሳያ የ6 ወር የባንክ ትራንዛክሽን ኢንድ ባላንስ 10 በመቶ በድርጃታቸው ስም ማቅረብ አለባቸው፤

(12) በቢሮው የደረጃ ሽግግር አፈፃፀም መመሪያ መሰረት ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ የሚሸጋገሩትን ለማበረታታት ሲባል የመስሪያ ቦታ/መሬት ወይም የክላስተር ማዕከላት ወይም ሸድ እንዲያገኙ ሲደረግ፤ አነስተኛ አምራች ኢንዱስትሪዎች ደግሞ ካላቸው አቅም አኳያ መንግስት በገነባው ክላስተር ማዕከል ወይም ሸድ ብቻ የሚስተናገዱ ይሆናል፤

(13) ለአምራች ኢንዱስትሪ የተሰጠን መሬት ግንባታው ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት መሸጥ፣ መለወጥ ወይም ለ3ኛ ወገን ማስተላለፍ አይቻልም፤

(14) በፒ.ኤል.ሲ እና በሽርክና ማህበር ስም ለአምራች ኢንዱስትሪ የተሰጠን መሬት ግንባታው ሙሉ በሙሉ ተጠናቆ ምርት ማምረት ከመጀመሩ በፊት ፕሮጀክቱ ሲገመገም በመመስረቻ ጽሁፍ እና መተዳደሪያ ደንብ ላይ ከነበሩት አባላት ውጭ በባለቤትነት ይዞ መገኘት አይቻልም፤

(15) ለአምራች ኢንዱስትሪ የተሰጠን የመስሪያ ቦታ/መሬት ለግለሰብ በብድር ወይም በሌላ እዳ ማስያዝ አይቻልም፡፡

(16) የተቋሙ ባለሙያ ለግምገማ የሚቀርብን ንግድ ስራ ዕቅድ/ፕሮጀክት በራሱ አዘጋጅቶ ከተገኘና ይህም በማስረጃ ሲረጋገጥ ህጋዊ እርምጃ የሚወሰድ ይሆናል፤

(17) በዚህ መመሪያ መስተናገድ የማይችሉ የኢንዱስትሪ ፕሮጀክቶች ካሉ በልዩ ሁኔታ በየደረጃው በሚገኘው የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም አስተያየት እየተሰጠ በክልሉ የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ በኩል የመጨረሻ ውሳኔ የሚያገኙ ይሆናል፡፡

18. መመሪያውን ስለማስፈፀም

(1) በየደረጃው የሚገኝ የኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ተቋም እና ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ባሉበት ከተሞች ኮርፖሬሽኑ ይህን መመሪያ ተፈጻሚ እንዲሆን ያደርጋል፡፡

(2) ይህን መመሪያ በመተግበር ሂደት አንድን ሰው አላግባብ ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት በማሰብ አላግባብ የተረጎመ በየደረጃው የሚገኝ የቢሮው ባለሙያ ወይም ኀላፊ አግባብ ባለው ሕግ መሠረት ተጠያቂ ይሆናል፡፡

19. መመሪያውን ስለማሻሻል

አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ቢሮው ይህን መመሪያ ሊያሻሽለው ይችላል፡፡

20. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ህጎች

(1) "በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ኢንዱስትሪና ኢንቨስትመንት ቢሮ ከአነስተኛ ወደ መካከለኛ ለተሸጋገሩ አምራች ኢንዱስትሪዎች የመስሪያ ቦታ ወይም መሬት አሰጣጥና መጠን ለመወሰን የወጣ መመሪያ ቁጥር 02/2013" በዚህ መመሪያ ተሽሯል፡፡

(2) ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማናቸውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር ይህ መመሪያ ከፀደቀበት ቀን ጀምሮ ተፈፃሚ አይሆንም፡፡

21. መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ

ይህ መመሪያ በቢሮው ኃላፊ ከተፈረመበት ከ ---- ቀን 2015 ዓ/ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡